ECIC
Ethio Cult Info Center
DEFENDING THE DEFENCELESS

ኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መከላከያና መረጃ መዐከል

http://www.saveethiopians.net

## ከዘመን አመጣሹ አታላይ መንፈስ እንጠበቅ ::

## TO BE FOREWARNED IS TO BE FOREARMED!
## አንብበው ለቤተሰብና ወዳጆችዎ በማስነበብ ከጥፋት ያስጠንቅቁ

ECIC – A/2008-C 08/05/18

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊ ወንድምና እህቶች ሰላም ለእናንት ይሁን ባላችሁበት:-

በቅርቡ በድርጅታችን የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መካላከያና መረጃ መዐከል Ethiopian Cult Information Center(ECIC) http://www.saveethiopians.net አማካኝነት የወጡ ቪዲዮዎች ለብዙዎቻችን በገሀድ እንዳሳዩት በሀይማኖት ሽፋን በዜጎች ላይ የሚደረገውን መጥፎ ድርጊት በስሙ ጠርቶ መጋለጥ ያለብት ደረጃ መድረሱን አሳይተውናል:: እኛም በድርጅታችን በኩል በተቋቋመ የቡድን አማካኝነት ይህንን ጉዳይ እንዴት አድርጎ በስፋትና በፍጥነት ህዝብን ማሳወቅ ማስጠንቀቅ ይቻላል የሚለውን ጉዳይ ከተወያየንበት በኋላ በሰለጠነው አለም እንደተለመደው ህዝባቸውን በፍጥነት አንዳንድ መጥፎ ድርጊቶችን ለማስጠንቀቅ የሚጠቀሙበትን ማስጠንቀቂያ „ALERT“ በመገናኛ ብዙሀን አማካኝነት ማውጣቱ ብዙዎች ሳያውቁ የዚህ አይነት ተመሳሳይ ጥፋት ተጠቂ እንዳይሆኑ ይረዳል ብለን ስላመንበት ከዚህ በታች የሚመለከተውን ጥፋት ተጠንቀቁ እንላለን::

ይህን ልንጠነቀቅበት የሚገባ መጥፎ ድርጊት በአዳዲስ መጤ ሀይማኖቶች በኩል እየሱስ ነኝ ቅብጥርሴ ነኝ ብሎ ከሚመጣ አይን አውጣ ክፉ መንፈስ የሚመጣ ሲሆን በተደጋጋሚ እንደታየው አሁንም ማንም ዜጋ በግልጽ በየጸበሉ በየስነ ልቦና ህክምና ቤቶች በመሄድ ማየትና ማረጋገጥ እንደሚችለው በእንደዚህ አይነት መጤ ስህተት እምነት በኩል የመጣ ራስ ወዳድ አይን አውጣ ክፉ መንፈስ ብዙውን ግዜ ሰዎች መጤ እምነቱን አላምንም አልፈልግም ብለው ሲወጡ ወይም አለመፈለጋቸውን ሲገልጹ በጣም የሚያስቸግርና የግለሰቦቹ ሰውነት ህይወት ውስጥ በመግባት ከውስጥ ልባቸውን ኩላሊታቸውን የተለያዩ የሰውነት ክፍላቸውን በማሳመም እንዲሁም በኑሯቸው ላይ በህይወታቸው ላይ ችግርን በማምጣት በመንደር ወይም በከተማ አቀፍ ሀይማኖታዊ መስለ ቲዎሪ ሽፋን ካላመናችሁኝ ወይም ጌታ አምላክ ባላችሁ ካልተቀበላችሁኝ በማለት የሚያስቸግር ነው:: ይህንን በተመለከት በአሁኑ ሰአት በየጸበሉ ከተለያየ የመናፍቃን ቡድን የወጡ ሰዎች የሚደርስባቸውን ወይም ወጥተው በሰላም ከመጤ ሀይማኖት ቲዎሪው ውጪ ልኑር ሲሉ በዚህ አመኑኝ ባይ ጋኔን ድርቅና የሚቸገሩ የብዙ ወገን ችግሮችን የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መካላከያና መረጃ መዐከል Ethiopian Cult Information Center(ECIC ) ድህረ ገጻችን ላይ በማየት ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል:: በተለይ የእንደዚህ አይነቱን የመጤ መናፍቃን ቡድን እየሱስ ነኝ ቅብጥርሴ ነኝ ባይ ጋኔን ባህሪይ ልዩ የሚያደርገው ሲጋለጥ ሰዎችን ዝም ለማሳኘት የሚያጠቃና ለማስፈራራት የሚሞክር ሲሆን በየመናፍቃኑ ቡድን በኩል እየሱስ ነኝ እያልኩ በየጸበሉ ጋኔን ነኝ በማለት ሳታልል ተያዝኩ ብሎ የማያፍርና በጥፋቱ የሚቀጥል መጥፎ አይን አውጣና ደረቅ መንፈስ መሆኑ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ከሰዎች ጋር በማስቸገር ድብብቆሽ ሊጫወት የሚፈልግ ተራ መንፈስ መሆኑ

ባህሪውን ልዩ ያደርጉታል:: ስለዚህ ድርጅታችን ኢትዮጵያውያኖችን ከእንደዚህ አይነት በ በተለያዩ መጤ መናፍቅ በኩል እየሱስ ነኝ እያለ በየጽበሉና መስኪዱ ጋኔን ነኝ ከሚል አታላይ በሰው ህይወት ላይ እንደፓራሳይት ከሚጣበቅና ከሚያስቸግር ተራ መንፈስ ራሳችሁን ጠበቁ:: ተጠንቀቁ ይላል::

በዚሁ አጋጣሚ ምን ያክል ዛሬ ኢትዮጵያውያኖች በውጪ ሀይሎች በሚመሩ ጎጂ አምልኮ ቡድኖች እንደተጠቁ ክብራቸው እንደተነካና ስለእነዚህ ጎጂ አምልኮ ቡድኖች ያላወቁ ቡድኖች በእነዚህ ቡድኖች ማታለል ሊጠመዱ እንደሚችሉ ማየት ይችሉ ዘንድ እነዚህ ቪዲዮዎች ከኢንተርኔት ላይ እንዲመለከቱ አደራ እንላለን:.

**http://www.youtube.com/watch?v=VD9ZKgUR25M**
**http://video.google.de/videoplay?docid=5371941839083108494**
**http://video.google.de/videoplay?docid=-8155637464973550729**
**http://www.myjesussaves.com/T8.html**
**http://ex-pentecostals.org/**
**http://www.bible.ca/tongues-encyclopedia-pentecostal-preachers.htm**

ብዙዎቻችሁ በኢሜልም እንደጠየቃችሁን ምን የሚሉት ድርቅና ነው ካላመኑ ብሎ ዜጎችን?

- የሰው ህይወት ላይ በአምልኮ ሽፋን እንደፓራሳይት ድርቅ ብሎ ማስቸገር?
- የሰው አካል(ልብ ኩላሊት ሳንባን.. ) ውስጥ ገብቶ ሰውን ከውስጥ ማስቸገር ማሳመም?
- የሰውን እንቅልፍ/እረፍት መንሳት?
- የሰውን ኑሮን ስራን ትዳርን ሰላም መንሳት?
- በየመናፍቅኑ ቤት እየሱስ ነኝ እያሉ ዜጎችን ካሰቃዩ በኋላ በየጸበሉ ሰይጣን ነኝ የሚሉት ቲያትር::

የእነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች መልስ እንደሰለጠነው ህብረተሰብ ማወቅ የምንችለው እንደዚህ ያሉ እውነቶች በማስጠንቀቂያ መልክ ወደ ህዝብ ሲወጡ ብቻ ነው::

ይህ ሀይማኖት ወይንም እምነት ሳይሆን ህብረተሰቡን ለባዕድ አገርን ለውርደት በመዳረግ ደካማና የተኮላሸ ህብረተሰብ ለማድረግ በምእራባውያን አቀንቃኝነት ባገራችን ኢትዮጵያና በሕዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን ታላቅ በደል ዛሬ ታግለን ከአገራችን ምድር በማስወጣት ወደመጣበት ባህር ማዶ ተመልሶ እንዲሄድ ማድረግ ካልቻልን ነገ ላገርና ለወገን ተቆርቋሪ ዜጋ ይኖራል ማለት አዳጋች ነው:: ስለሆነም ይህ በህብረተሰባችን ላይ የሚያደርሱትን ኢሰብአዊ ድርጊት እንደሆነ ታውቆና ታምኖበት አገርንና ወገንን ለማዳን ሁሉም አገር ወዳድ የሚዲያ ክፍሎች ይህንን አድራጎት በጥብቅ በማውገዝና ህብረተሰቡንም በማስተማር የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ ሊተባበር ይገባል::

ከዚህም አንጻር ህዝባዊ ሚዲያዎችን እርዳታ በመጠየቅ ድህረ ገጻችንን http://www.saveethiopians.net ለህዝብ ማሳወቁ አስፈላጊ ነው ብለን ለጋራ ጉዳይ ትብብራችሁን እንጠይቃለን:: የድህረ ገጻችንን አዳራሻና ስለድህረ ገጻችን መጠነኛ ሪፖርት በመዘገብ በጋዜጣችሁ በመጽሄታችሁ ላይ በሚመቻችሁ መልክ በማተም ያላወቀ ህዝባችንን ህዝብ ስለዚህ ነገር ጥንቃቄ እንዲያረግ በማሳወቁ ተባበሩን:: ውለታውን ሳይማር ያስተማረን ህዝብ አምላክ ሁላችንንም ይክፈል:: የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መካላከያና መረጃ መዐከል (Ethiopian Cult Information Center( ECIC) አዳራሻ http://www.saveethiopians.net

አገራችን ኢትዮጵያን ስላም ያቆይልን,
የድርጅቱ የህዝብ መገናኛ ክፍል
<u>ከኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መካላከያና መረጃ መዐከል</u>
Ethiopian Cult Information Center (ECIC ) http://www.saveethiopians.net